MINNESOTA
FOR MARRIAGE

ONE MAN, ONE WOMAN
WWW.MINNESOTAFORMARRIAGE.COM

# የትዳርን ትርጓሜ መጠበቅ አስፈላጊነት

የትዳር ትርጓሜን የተንተራሰ ክርክር ላለፉት አመታት አነጋጋሪ ርዕስ ከመሆኑም ባለፈ የህዝብ ድምፅ ይሰጥበት ዘንድ በ2012 ዓ.ም በሚደረገው ምርጫ ላይ ለውሳኔ-ህዝብ(referendum) ይቀርብ ዘንድ ተወስኗል።

ነገርግን የዚህ አነጋጋሪ ጉዳይ ሥር መሰረቱ ምን ይሆን?በህብረተሰብ እና በመጪው ትውልድ ላይስ የሚኖረው ትፅዕኖ ምን ይሆን? የመጪውስ ህዝበ-ውሳኔ ውጤት ምን ለውጥን ይዞ ይመጣ ይሆን? የሚለውን ማገናዘብ ጠቀሜታ አለው።

ለመጪው ህዝበ-ውሳኔ የሚቀርቡት <u>ተወዳዳሪ</u> ሃሳቦች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም በግብረ-ሰዶማዊ ትዳር ደጋፊዎች የሚቀርበው ትዳር ፆታን ያላማከለ የማንኛውም ሁለት ሰዎች ውህደት የማድረግ ሀሳብ እና አሊያም ደግሞ በአሜሪካ ህገ-መንግስት ሰፍሮ እንዳለው እና ዓለም-ኣቀፋዊ መረዳት ሆኖ በሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ እንደዘለቀው <u>**ትዳር የአንድ ወንድ እና የአንድ ሴት ጥምረት እንደሆነ የመጠበቅ**</u> ሁለት ሐሳቦች ናቸው።

ከእነዚህ ሁለት ሃሳቦች አንዱ በህዝብ ምርጫ አግኝቶ በህግ የሚፀድቅ ሲሆን ፣ ይኸውም ለወደፊት ትዳርን በተመለከተ ለሚኖር አስተሳሰብ መሰረት ሆኖ ማገልገሉ የማይካድ ነው።

በዚህ ኣጋጣሚ ለምን የትዳር ትርጉም በዓለም-አቀፈያዊ ይዘቱ በሁለት ተቃራኒ ፆቶች መሐል የሚደረግ ውሕደት መሆኑ እንደታመነበት መጠየቁ ጥሩ ይሆናል። ምላሹም በኣጭር ቃል <u>ልጆች</u> የሚል ይሆናል። ትዳር እጅግ ልዩ የሆነ የሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ህብረት በመሆኑ በዚህ ልዩ ህብረት ውስጥ ባለው ሂደት <u>***ዘርን የመተካት አቅም***</u> እንዳለው ይገለፃል። ትዳር የህብረተሰብን ቀጣይነት ማስፈፅሚያ መንገድ ለመሆኑም ማመላከቻው ልጅን የማፍራትና የመንከባከብ ብሎም የመጠበቁ ሃላፊነት እንዳለው ተጠቃሽ መሆን ይችላል። አንድ ወንድ እና ሴትን ትዳር እንዲመሰርቱ በማበረታታት የሚፈጠሩትን ልጆች የማንነት መለያ ከወላጆቻቸው እንዲያገኙ እድልን እንፈጥራለን። በአጠቃላይ ምንም እንኳን ፍቺ እና ሞት ትዳርን ቢያደናቅፉትም ወላጅ እናት እና ኣባት ለልጅ ዕድገት እጅግ ወሳኝነት ኣላቸው።

**በሌሎች 31 እስቴቶች እንደተወሰነው ሁሉ በሚቀጥለው ምርጫ በሚኔሶታ(Mennesota) November, 2012 የሚፀድቀው የህዝብ ውሳኔ ብልጫን ካገኘ አሁን በሥራ ላይ ያለውን ህግ የትዳርን ትርጉም(የአንድ ወንድ እና ሴት ጥምረት) ቀጣይነትና መሰረታዊነቱን እንደጠበቀ እንዲቀጥል ያስችላል።**

በተጨማሪም የዚህ ህግ መጽደቅ የህዝብን ውሳኔ በማንፀባረቅ በተወሰኑ አነሳሺ ሀይላት(activists) እና በጥቂት ህግ ኣዋቂዎች የሚያደረገውን ጥረት ያኮላሻል።

ትዳር በኣንድ ወንድ እና ሴት መሐል በመሆኑ ቤተሰብ እና ልጆች ብሎም ሕብረተሰባችን ተጠቃሚ ይሆናል። በ2012 ዓ.ም የሚደረገውም ትዳርን ያማከለው የህዝብ ምርጫ ይህንን እጅግ ወሳኝ የሆነ የህብረተሰብ አካል ይህውም ትዳርን እንጠብቅ ዘንድ እድሉን ይሰጠናል።

ስም

ኢሜል ኣድራሻ

ስልክ ቁጥር

የመኖሪያ ኣድራሻ

ከተማ ስቴት ዚፐ ኮድ

የቤተ-ክርስቲያንዎ ስም

የሚገኝበት ከተማ

# ትዳርን የተጋፈጠው አደጋ

በሚኒሶታ የሚደረገው የትዳርን ትርጉም የመቀየር ሙከራ በሃሳቡ ደጋፊዎቹ እና በጥቂት ፖለቲከኞች ተጠናክሮ ቀጥሏል። እነዚህ ደጋፊዎች እና ፖለቲከኞች ስኬት ያገኙ እንደሆነ እጅግ ትልቅ የሆነን ተፅዕኖ በቤተ-ክርስቲያን፣ በጥቃቅን የንግድ ማዕከሎች፣ በተለያዩ ግለ-ሰቦች እና ባጠቃላይ በሕብረተሰባችን ላይ ማምጣታቸው እውን ይሆናል።

አዲሱን የትዳር ትርጉም የማይቀበሉ ሁሉ እንደ ዘረኛ እና እንደ አግላይ ተቆጥረው ላመኑበት ሃሳብ በህግ ተጠያቂነት ስር ይውላሉ። ይህም በሌሎች እስቴቶች መሆን ጀምሯል። ለምሳሌ:-

- ለተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ በራቸውን ዝግ ያደረጉ  የሃይማኖት ተቋማት የከ ቀረጥ-ነፃ(Tax Free) መብታቸው ተገፏል።
- የሃይማኖት ድርጅቶች ለምሳሌ፡ በቦስተን እና በዋሺንግተን-ዲሲ ባሉት የካቶሊክ እርዳታ መስጪያ ድርጅቶች አዲሱን የትዳር አስተያየት በመቀበል አሊያም እንደ እምነታቸው ሕብረተሰብን በማገልገል ምርጫ ውስጥ በመውደቅ በስተመጨረሻ ተዘግተዋል።
- በትምህርት ቤት ለህፃናት የሚተላለፈው ትዳርን ያስመለከተ ትምህርት ፆታን ያለየ እንዲሆን ያስገድዳል። በማሳቹሴትስ(Massachusetts) የ2 ዓመት ህፃናት ሳይቀሩ የዚህ አዲስ ትምህርት አካል እንዲሆኑ ሆኗል። ፍርድ ቤቶችም አስቀድሞ ልጆችን የማስጠንቀቅ አሊያም ልጆቻቸውን እንዲህ ካለ ትምህርት-ቤት የማስቀረትን መብትን ከወላጆች ገፏል።
-  የሰርግ ባለሞያዎች በተመሳሳይ ፆታ ተጋቢዎች ሰርግ ላይ ላለመገኘት በመወሰናቸው ተቀተዋል።
- እንደ ዶክተር፣ ጠበቃ፣አካውንታንት የመሳሰሉ በመንግሥት ፍቃድ የሚሰሩ ስራዎች የፍቃድ መነጠቅ አደጋን ትጋፍጠዋል። ለምሳሌ አንድ አማካሪ የተመሳሳይ ፆታ ተጋቢዎችን ከማስትናገድ ወደ ኃላ ማለት አይችልም። አለዚያም የመስሪያ ፍቃዱን እና እምነቱን አደጋ ላይ ይጥላል።
- በሚኔሶታ የሚኖሩ፣ ትዳር በአንድ ወንድ እና አንድ ሴት መሃል መሆኑን የሚያምኑ ሁሉ እንደ ዘረኛ ሆነው ህግ ፊት እንዲገኙ ያደርጋል። ይህ ህግ የጥንቱን ትዳር ደጋፊዎች ከመቅጣቱም ባለፈ የግብርሰዶማዊውን አስተያየት ለማሰራጨት ያግዛል።
- በአጠቃላይ ህጋችን ለቤተሰብ እና ልጆች የቆመ መሆኑ ቀርቶ በተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ለተጠመዱ ጥቂቶች የቆመ ይሆናል ማለት ነው።